# ጥናት አንድ (ማርቆስ 14፤ 3-9)

የጥናቱ ዓላማ፡- ለኢየሱስ በምንሰዋው መስዋዕት የሰዎችን ይሉኝታና ነቀፋ ሳንፈራ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት እስካለው ድረስ ወደኋላ ሳንል መስዋዕታችንን ማቅረብ እንደሚኖርብን ለመማር።

**የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እርስዋ ማድረግ የምትችለውን ያህል አድርጋለች› ማር 14፡8**

1. ይህች ሴት በጌታ ራስ ላይ ስላፈሰሰችው የሽቱ ዓይነት ከምንባቡ የምትረዳቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. ለምንድነው አንዳንዶች ሴትየዋ ያደረገችውን ነገር እንደጥፋት የቆጠሩበት ምክንያት? ለክሳቸው የጌታ መልስ ምን ነበረ?
3. በክፍሉ ውስጥ ከምናየው፤ ሽቶው ተሸጦ ለድሆች መሰጠቱን ጌታ የተቃወመበት ምክንያት ምን እንደነበረ ግለጽ።
4. በዮሐ 12፡1-8 ውስጥ ዮሐንስ በሴትየዋ ላይ ከቀረበው ተቃውሞ በስተጀርባ ስለነበረው ስውር ምክንያት የሚናገረው ነገር ምንድነው?
5. ሌሎቹ በዚያ የተሰበሰቡት ሰዎች ለኢየሱስ ያደረጉለትን ነገር ይህች ሴት ካደረገችለት ነገር ጋራ አወዳድር። ከዚህች ሴት ድርጊት እዚያ የተሰበሰቡት ሰዎች ምን መማር ይችሉ ነበር ትላለህ? ከዚያ ይልቅ ግን የመረጡት ምን ነበረ?
6. በዚህ ስፍራ ‹‹…እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋራ አልኖርም›› በሌላ ስፍራ ደግሞ ጌታ ሁልጊዜ ከልጆቹ ጋራ እንዳለ ይናገራል። መጽሃፍ ቅዱሳችን የማይቃረን ከሆነ ታዲያ በዚህ ሥፍራ ይህንን ማለቱ ምን ለማለት ፈልጎ ነው ትላለህ?
7. ይህች ሴት ያደረገችው ድርጊት ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ መታሰቢያ ሆኖ መነገሩ ምን ያስተምርሃል?
8. በህይወትህ ለእግዚአብሄ ወይም ለጌታ ቤት ባደረከው ነገር ነቀፋ ደርሶብህ ያውቃል ወይ? አንተስ ሰዎች ለጌታ የሚችሉትን በሰጡ ጊዜ ነቅፈህ ታውቃለህ ወይ? ለአምልኮህ አስከምን ድረስ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነህ?

# ጥናት ሁለት (ሉቃስ 7 ፤36-43)

**የጥናቱ አላማ፡** ከይሉኝታ ጋር ጌታን ማምለክ አስቸጋሪ እንደሆነና ሰውን ከመፍራት ካልተላቀቅን እውነተኛ አምልኮ እንደማይቻል ለመማር።

**የምናሰላስለው ጥቅስ፡** «ከበስተ ኋላው እግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፤ በራሷም ጠጉር ታብሰው ጀመር፤ እግሩንም እየሳመች ሽቱውን ቀባችው።» ሉቃ 7:38

1. **በቅድሚያ ሉቃስ** 7:36-43 **በአንድነት ይነበብ። የታሪኩን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የተነበበውን ክፍል በራስህ መንገድ ታሪኩን ተርክ።** ከሁለት ላልበለጡ **ሰዎች እድል ይሰጥ።**
2. **በቁጥር** 37 **ላይ "አንዲት ሃጢያተኛ ሴት"** ሲል ይናገራል። **ይህችን ሴት ሃጥያተኛ ለመባል ያበቃት ነገር ምንድነው ትላለህ?**
3. **በዚህ በተነበበው ክፍል ውስጥ ፈርሳዊውና ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሃጢያተኛይቱ ሴት ያላቸውን አመለካከት አነጻጽር። ሰዎች እኛን የሚያዩበትና ኢየሱስ ስለሚያይበት መንገድ ይህ ክፍል የሚያሳየን ምንድነው?**
4. ራስ በሽቶ እንደቀባች፤ **እግሩንም በእንባዋ** እያራሰች በጸጉሯ እንዳበሰችው ክፍሉ ይነግረናል። ይህ አባባል ስለ ስጦታዋ አይነትና ጥራት ምን ያሳያል?
5. ቁ **39** ላይ «የጠራው ፈሪሳዊውም:- አይቶ ይህስ ነብይ ቢሆን...» የሚለው አባባል ስለ ፈሪሳዊው የሚያረጋግጥልን አንድ ትልቅ እውነት ምንድነው?
6. ቁ39 ላይ ‹‹ብሎ በልቡ አሰበ›› ይላል። ፈሪሳዊው በልቡ ያሰበውን ማወቁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶሰ የሚነግረን ነገር ምንድነው?
7. ይህች ሴት ግብዣውን አበላሽታበታለች፣የግብዣውን ሥርዓት አልጠበቀችም፣አለባበሷም ምናልባት የአለባበሱን ወግ የተከተለ አይደለም። ኢየሱስ ታዲያ ይህንን ሁሉ እያወቀ እንዴት የሰው ግብዣ ሲበላሽ ዝም ብሎ ያስተናግዳታል?
8. ስፍራ ሳትመርጥ በሰው ግብዣ ውስጥ እንኳን ገብታ ይህንን ለማድረግ መወሰኗ ለኛ ምን ያስተምረናል? የሰዎቹ ብዛትና መንፈሳዊ መስለው መቅረባቸው አላስፈራትም። ይህ ለምን ይመስልሃል?
9. የዚህች ሴት አምልኮ ከአምልኮህ በምን እንደሚለይ ወይም በምን እንደሚመሳሰል ተናገር። በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ይሉኝታ በአምልኮህ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ አለው? ከሴትየዋ በተማርከው ትምህርት እንዴት መለወጥ እንደምታስብ ተናገር።

# ጥናት ሶስት (ሉቃስ 7:44-50)

የጥቱ ዓላማ፦ አማኞች ከእግዚአብሄር ብዙ እንደተቀብሉ እንገነዘቡና ከልብ በመነጨ ፍቅር የምስጋና መስዋዕት እንዲያቀርቡ ለማነቃቃት።
የምናሰላስለው ጥቅስ፦ «ስለዚህ እልሃለሁ፤ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ሐጥያትዋ ተሰርዮላታል።» ሉቃስ 7:47

1. በህይወትህ የእግዚአብሄርን ፍቅር ለመግለጽ በግልህ የምትጠቀምባቸውን የራስህ የሆኑ መንገዶች ካሉህ ለወገኖች አካፍል።
2. ሉቃስ 7:44-50ን በማንበብ ፈሪሳዊው ለጌታ ማድረግ የሚገባው ነገር ግን ያላደረጋቸውን ነግሮች ዘርዝር። በተቃራኒው ደግሞ ሐጥያተኛ የተባለችው ሴት ያደረገቻቸውን ነገሮች ዘርዝር።
3. በአንተ ግምት ለምንድነው ይህ ፈሪሳዊ ከላይ የዘረዘርናቸውን ነገሮች ለጌታ ያላደረገለት?
4. ፈሪሳዊው ወደ ቤቱ ኢየሱስን ጋብዟል፣ ሰዎችን ለማብላት ገንዘቡንና ጊዜውን ሁሉ አውጥቷል። ታዲያ ለምንድነው የጌታ ትኩረት ፈሪሳዊውን ትቶ በሴትየዋ ላይ የሆነው? ይህ ሁኔታ አገልግሎትንና አምልኮን አስመልክቶ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
5. «ስለዚህ እልሃለሁ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ሐጥያትዋ ተሰርዮላታል» ቁ 47 ከዚህ አባባል የምትረዳው ነገር ምንድነው?
6. በቁጥር 47 ላይ ጌታ «ጥቂት የሚሰረይለት ጥቂተ ይወዳል» ሲል የሴቲቱ ሐጥያት ከፈሪሳዊው ይበልጣል ማለቱ ነው ወይ? ካለሆነስ ምን ማለቱ ነው?
7. በቁጥር 48-50 ባለው ውስጥ ይህች ሴት እጅግ በመውደዷ ከጌታ የተቀበለቻቸውን ሶስት ነገሮች ዘርዝር።
8. እግዚአብሄርን በብዙየሚወድና በጥቂት የሚወድ ሰው መለያው ምን ይሆናል ብለህ ታምናለህ? አንተስ ከሁለቱ አይነት ሰዎች ራስህን ከየትኛው ወገን ታስቀምጣለህ? ፍቅርህንስ እንዴትና በምን ሁኔታ እየገለጽክ ትገኛለህ?
9. ፈሪሳዊውንና ሐጥያተኛይቱን በማነጻጸር ለህይወትህ የተማርከውን ነገር ለወገኖች አካፍል።